# በስካር፣ በንዴትና በአስገዳጅ ሁኔታ የተፈጸሙ ወንጀሎች ኢ-ኃላፊነት በዐፄ ኢያሱ እና በዐፄ ዳዊት ሣልሳዊ ፍርዶች ውስጥ፡ ምልከታ ከታሪክ ማኅደር

*ነጋ እውነቴ መኮንን**

## አኅጽሮተ ጥናት

*በኢትዮጵያ ዘመናዊ የፍትሕ አስተዳደር ከመጀመሩ በፊት በወንጀል ጉዳዮች ላይ ይሰጡ የነበሩ ፍርዶች ለነገሥታቱ ችሎት ቀርበው የነገሥታቱ የመጨረሻ ይሁንታና ትንታኔ ያርፍባቸው የነበረ ሲሆን እስከ 1967 ዓ.ም ድረስ የቀጠለው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የዙፋን ችሎት በዋናነት ተጠቃሽ ነው። ነገሥታቱ የሚሰጧቸው ፍርዶች በአብዛኛው በዚህ ዘመን በብዙ አገራት የወንጀል ሕግጋት ውስጥ እውቅና አግኝተው ሥራ ላይ የዋሉ የወንጀል ሕግ መርኆችንና ጽንሰ-ሃሳቦችን ያንጸባርቁ ነበር። ይህ ምልከታ ለዐፄ ኢያሱ እና ለዐፄ ዳዊት ሣልሳዊ ችሎቶች የቀረቡ ሦስት ጉዳዮች የሚዳሰሱበት ሲሆን በሁለቱ ነገሥታት ፍርዶች ውስጥ የተነሱት በስካር፣ በንዴትና በአስገዳጅ ሁኔታ የሚፈጸሙ ወንጀሎችና መከራከሪያዎች ከዘመናዊው የወንጀል ኃላፊነት መከላከያ መርኆች ጋር የሚጣጣሙ ናቸው በማለት ፀሀፊው ይከራከራል።*

**ቁልፍ ቃላት፡** ስካር፣ ንዴት፣ አስገዳጅ ሁኔታ፣ ጥፋትን ማመን፣ የነገሥታት ፍርዶች፣ የወንጀል ኢ-ኃላፊነት

## *መግቢያ*

በኢትዮጵያ ዘመናዊ ሕግ ተቀርጾ ዘመናዊ የፍትሕ አስተዳደር ከመጀመሩ በፊት ይሰጡ የነበሩ ፍርዶች በአብዛኛው የነገሥታቱ የመጨረሻ ይሁንታና ትንታኔ ያረፈባቸው ነበሩ።[1] ይህ ሁኔታ በተወሰነ መልኩ እስከ 1967 ዓ.ም ድረስ የቀጠለ ሲሆን በዋናነት የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የዙፋን ችሎት ተጠቃሽ ነው። ለነገሥታቱ የሚቀርቡ ጉዳዮች በአብዛኛው የወንጀል ጉዳዮች ሲሆኑ የሚሰጧቸው ፍርዶች በዚህ ዘመን በብዙ አገራት የወንጀል ሕግጋት ውስጥ እውቅና አግኝተው ሥራ ላይ የዋሉ የወንጀል ሕግ መርኆችና ጽንሰ-ሃሳቦችን ያንጸባርቁ ነበር።

---

* በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሕግ ት/ቤት የሕግ ተባባሪ ፕሮፌሰር። ኤል ኤል ቢ.(አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በ1996 ዓ.ም)፣ ኤል ኤል ኤም (ዩኒቨርሲቲ ኦፍ ግሮኒንገን፣ ዘኔዘርላንድስ በ2000 ዓ.ም)፣ ከፍተኛ ዲፕሎማ በማስተማር ሥነ-ዘዴ (ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በ2007 ዓ.ም)፣ የፒ ኤቹ ዲ ተማሪ (ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ)፤ ፀሀፊውን በኢ-ሜይል አድራሻው beleteeng@yahoo.com ማግኘት ይቻላል።

[1] በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ዘመናዊ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የወጣው በ1923 ዓ.ም ሲሆን እስከ 1923 ዓ.ም ድረስ ለወንጀልና ለፍትሐ ብሔር ጉዳዮች ሕግ ሆኖ ያገለግል የነበረው ፍትሐ ነገሥት ነበር። አዲሱ የ1923 ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሙሉ በሙሉ ከነባሩ ፍትሐ ነገሥት ያፈነገጠ አዲስ ሕግ ሳይሆን ከፍትሐ ነገሥቱ የተወሰዱ ድንጋጌዎች የነበሩትና ከነባሩ ሕግ ጋር ተጣጥሞ ሥራ ላይ እንዲውል የተደረገ ነው። ይህንን በተመለከተ በ1923 ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በመቅድሙ ቁጥር 4 ሥር የሚከተለውን አስፍሮ እናገኘዋለን "[…] ወንጀሉና ቅጣቱ ተለያይቶ ታውቆ ይህነን የመሰለው ችግር ሁሉ እንዲቀር ሕዝቡም ሕጉ የሚከለክለውንና የማይከለክለውን ያለ ችግር ለመለየት እንዲችል የአውሮፓንም ሥርዓት እየተማረ ወደ ትልቅ የእውቀት ደረጃ እንዲደርስ እስካሁን ባገሩ የቆየውን ሥርዓት ሳንለውጥ የእኛም የፍትሐ ነገሥት መሠረቱ ከአውሮፓ ፍትሐ ነገሥት ጋራ በብዙ ሥፍራ ይገጥማልና ሁለቱን እያስማማን በ1923 ዓመት ይህንን ደንብ አቁመናል።" ከዚህ ጋር የተያዘና በሌሎች ጉዳዮች ላይ የበለጠ መረጃ መረጃ ለማገኘት የወንጀለኛ መቅጫ ደንብ፣(ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ)፣ 1923 ዓ.ም ይመለከቷል።

ከእነዚህ የወንጀል ሕግ መርኖችና ጽንሰ-ሃሳቦች መካከል አንድ ሰው በስካርም ይሁን በሌላ የአዕምሮን የማሰብና የማመዛዘን ችሎታ በሚቀንስ ምክንያት ወንጀል ከፈጸመ ከወንጀል ኃላፊነት ነጻ የሚሆንበት ይገኝበታል። ከዚህ በተጨማሪ የወንጀል ድርጊቱ የተፈጸመው በችግር ወይም በቁሳዊ እጦት ከሆነ፣ ወንጀለኛው ወንጀሉን የፈጸመው በንዴት ተነሳስቶ ከሆነና እንዲሁም ወንጀለኛው የተከሰሰበትን ጉዳይ ካመነ ቅጣቱ የሚቀልበት ከዚያም አልፎ በነጻ የሚሰናበትባቸው አጋጣሚዎች ነበሩ።

ወደ ጥናቱ ይዘት ስንመጣ በመጀመሪያ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ከወንጀል ኃላፊነት ነጻ የሚያደርጉ ምክንያቶች ይዘትና ምንነት፣ በሌሎች አገራት ሕግጋት ውስጥ የነበራቸውና ያላቸው ቦታ ምን እንደሚመስል ምልከታውን መረዳት በሚያስችል መልኩ አጭር ዳሰሳ ይደረጋል። በሌሎች አገራት ሕግጋት ላይ የሚደረገው ዳሰሳ ከሕግጋቱ ወቅታዊ ይዘት ይልቅ በዋናነት ታሪካዊ ዳራቸውና አመጣጣቸው ላይ ያተኩራል። ይህን የመረጠበት ምክንያት እነዚህን ሕግጋት ከሦስት መቶ አመታት በፊት በኢትዮጵያ ነገሥታት ከተሰጡ ፍርዶች ጋር በዘመን አቻነት ለማነጻጸር ይበልጥ ይጠቅማል በሚል ነው። ከዚህ በመቀጠል እነዚህ መርኖችና ጽንሰ-ሃሳቦች በሁለት የጎንደር ነገሥታት ማለትም በዐፄ ኢያሱ እና በዐፄ ዳዊት ሣልሳዊ በተሰጡ ፍርዶች ውስጥ የነበራቸውን ቦታ እንመለከታለን። በዐፄ ኢያሱ የተሰጡት ፍርዶች ሁለት ሲሆኑ የመጀመሪያው በስካር የተፈጸመ ወንጀል ሲሆን ሁለተኛው ፍርድ ቁሳዊ እጦትና ንዴት እንዲሁም የተከሰሱበትን ወንጀል ማመን ከወንጀል ኃላፊነት ነጻ እንደሚያደርጉ የሚያመላክት ነው። በዐፄ ዳዊት የተሰጠው ፍርድ ለዐፄ ኢያሱ ከቀረበላቸው የመጀመሪያው ጉዳይ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን በስካር የተፈጸመ ወንጀል የወንጀል ኃላፊነት እንደማያስከትል የሚያሳይ ነው። እነዚህ የተጠቀሱት ሁለት ነገሥታት የተመረጡት ለጊዜው ለጉዳዩ ጠቃሚ ሆነው የሁለቱ ነገሥታት ፍርዶች ብቻ በመሆናቸው ነው። በመጨረሻም ጥናቱ የማጠቃለያ ነጥቦችን በማንሳት ይቋጫል።

## 1. በስካር ሁኔታ/መንፈስ የተፈጸመ ወንጀል ኢ-ኃላፊነት በሌሎች አገራት ሕግጋት ውስጥ ያለው ቦታ፦ አጭር ዳሰሳ

በስካርና በሌሎች የአዕምሮ ህመም ወይም ችግሮች ሳቢያ ወንጀል የሚፈጸሙ ሰዎችን ከወንጀል ኃላፊነት ነጻ ማድረግ በጥንታዊ ሕግጋት ውስጥ እውቅና ተሰጥቶት ሲሠራበት የኖረ ነው። ጉዳዩ ከጥንታዊ ሕግጋት በተጨማሪ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም ተጠቅሶ እናገኘዋለን።[2] በስካር የተፈጸመ ወንጀል ከኃፊነት ነጻ የሚያደርግበት መሠረታዊ ምክንያት አጥፊው አዕምሮው በአልኮልም ሆነ በሌሎች አደንዛዥ ነገሮች ከተበረዘ ጥሩን ከመጥፎ፣ ትክክለኛን ነገር ከስህተት የመለየት፣ የማመዛዘንና የመወሰን አቅሙ ይዳከማል ወይም ጨርሶ ይጠፋል ከሚል እሳቤ የመጣ ነው።[3] በእነዚህና በሌሎች ምክንያቶች የአዕምሮው

[2] Gabriel Hallevy, The Matrix of Insanity in Modern Criminal Law, (Springer, Newyork, Dordrecht, London), 139 (2015). ፕሮፌሰር ሀልቨይ ይህንን ጉዳይ ለማብራራት በመጽሐፍ ቅዱስ ዘፍጥረት 9፣ 20-27ና 19፤31-38 ድረስ ያለውን በምሳሌነት ይጠቅሳሉ።

[3] Finbarr McAuley, The Intoxication Defense in Criminal Law, 32 Irish Jurist (N.S.) 244 (1997).

የማመዛዘን አቅም ተዳክሞ ወይም ጠፍቶ ወንጀል የፈጸመ ሰው አስቦ (intentionally) ወንጀል ፈጽሟል ስለማይባል የወንጀል ኃላፊነት የለበትም፡፡[4]

ቀደም ባሉት ጊዜያት በተለይም ከ16ኛው ክፍለ ዘመን በፊት የኮመን ሎው የሕግ ሥርዓት በሚከተሉ አገራት በዋናነት በእንግሊዝ በስካር የተፈጸመ ወንጀል ከኃላፊነት ነጻ ለመሆን እንደመከራከሪያ አያገለግልም ነበር፡፡[5] በተለይ ከ19ኛው ክፍለ ዘመን በፊት በእነዚህ አገራት በስካር የተፈጸመ ወንጀል ከኃላፊነት ነጻ ለመሆን እንደመከራከሪያ ሳይሆን ክስን በተቃራኒው ለማክበድ ያገለግል ነበር፡፡[6] በዘመኑ በእነዚህ አገራት ስካር እንደ ወንጀል ባይቆጠርም እንደ መጥፎ ድርጊትና ከሞራል ያፈነገጠ ተግባር ተደርጎ ይቆጠር ነበር፡፡[7] ተከሳሽ ስካርን ከኃላፊነት ነጻ ለመሆን እንደ መከራከሪያ እንዲያቀርብ መፍቀድ ቅጣት አልባ አስከፊ ወንጀሎችን እንዲፈጽም የሚያስችል በር እንደ መክፈት ይቆጠራል የሚል መከራከሪያ ይቀርብ ነበር፡፡[8] ነገር ግን ጉዳዩ በሂደትና ቀስ በቀስ የፍርድ ቤቶችን ትኩረት እያገኘ መጥቶ ለመጀመሪያ ጊዜ እ.አ.አ. በ1819 የእንግሊዝ ፍርድ ቤትን እውቅና አገኘ፡፡[9] ቢሆንም ይህ እንደ ብቸኛ ክስተት ሊቆጠር የሚችል የፍርድ ቤት ውሳኔ ዳብሮና በስፋት እውቅና አግኝቶ በእንግሊዝና በሌሎች የኮመን ሎው አገራት ሕግ ለመሆንና በቶሎ ሥር ለመስደድ ጊዜ ወስዶበታል፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ በተለያየ ጊዜ የቀረበላቸው የአሜሪካ ፍርድ ቤቶች በስካር የተፈጸመ ወንጀል ከኃላፊነት ነጻ ያደርጋል የሚል ውሳኔ ላይ ለመድረስ አልቻሉም ነበር፡፡[10] ነገር ግን እ.አ.አ. በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ጀምሮ በስካርና በሌሎች አደንዛዥ ነገሮች የተፈጸመ ወንጀል ከኃላፊነት ነጻ እንደሚያደርግ የፍርድ ቤቶችን እውቅና እያገኘ መጥቷል፡፡[11]

በስካር የተፈጸመ ወንጀል የአህጉረ አውሮፓ የሲቪል ሎው ሕግ ሥርዓትን በሚከተለው የፈረንሳይ ሕግ ያለውን ቦታ ስንመለከት እ.አ.አ. እስከ 1957 ድረስ በስካር የተፈጸመ ወንጀል ከኃላፊነት ነጻ ለመሆን እንደመከራከሪያ አይቀርብም ነበር፡፡[12] ከ1957 ዓ.ም በኋላ ግን ሕጉ ቀስ በቀስ እየላላ መጥቶ ስካር አንድን ሰው ራሱን ሙሉ በሙሉ

---

[4] በዚህ ዘመን በሁሉም አገራት የወንጀል ሕግጋት ውስጥ አንድ ሰው የወንጀል ኃላፊነት የሚኖርበት ሦስት ነገሮች ተሟልተው ሲገኙ ሲሆን እነሱም፦ ጉዳዩ በሕግ ወንጀል ወይም ሕገወጥ ሆኖ የተከለከለ መሆን ይኖርበታል፣ ሁለተኛው ይህንን ሕገወጥ ሆኖ በሕግ የተከለከለ ጉዳይ በድርጊት ወይም በግድፈት መጣስ ይኖርበታል፣ ሦስተኛውና ከያዝነው ጉዳይ ጋር የሚገናኘው ክፍል የሃሳብ ክፍል ሲሆን ይህም ድርጊቱ ወይም ግድፈቱ ሆነ ተብሎ ወይም በግዴለሽነት መፈጸም ይኖርበታል፡፡

[5] Kyndra K. Miller, Criminal Law - Intoxication as a Defense: The Drunk and Dangerous Model - Montana v. Egelhoff, 33 Land & Water L. Rev. 751 (1998).

[6] Charles W. Smith, Intoxication as a Defense to a Criminal Charge in Pennsylvania, 76 Dick. L. Rev. 16 (1971).

[7] ዝኒ ከማሁ፡፡

[8] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 16-17፡፡

[9] ኪንደራ ኬ ሚለር፣ ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 5፣ ገጽ 715፡፡ ፍርድ ቤቱ ይህንን እውቅና የሰጠው በKing v. Grindley ሲሆን ጉዳዩን እደሚከተለው ተመልክቶታል፦ “though voluntary drunkness cannot excuse from the commissioin of crime, yet where, as on a charge of murder, the material question is, whether an act was premeditated or done with sudden heat or impulse, <u>the fact of the party being intoxicated is a circumstance proper to be taken into consideration.</u>” (የማስመር አጽንኦት በአጥኚው የተጨመረበት፡፡)

[10] The Missouri Supreme Court in State vs. Cross, 1858, the Vermont Suprme Court in State vs. Tatro, 1878 እንደምሳሌ መጥቀስ ይቻላል፡፡

[11] ለምሳሌ Hopt vs. People, 1882 መመልከት ይቻላል፡፡

[12] Alan Reed, Michael Bohlander, Nicola Wake, and Emma Smith(eds.), General Defense in Criminal Law, Domestic and Comparative Perspectives, (Ashgate Publishing Limited, Burlington), 223 (2014).

ወደማይቆጣጠርበት ደረጃ ካደረሰው እንደ አዕምሮ ሕመምተኛ ተቆጥሮ ከወንጀል ኃላፊነት ነጻ የሚሆንበት ሁኔታ ተፈጥሯል።[13] ነገር ግን እ.አ.አ. 2007 በወጣው ሕግ መሠረት በመጠጥና በአደንዛዥ ዕጽ ተገፋፍተው የሚፈጸሙ ወሲባዊ ወንጀሎችን በተመለከተ ስካር በተቃራኒው የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ሆኖ ተደንግጓል። ከዚህ ሕግ በስተጀርባ ያለው ምክንያት ከሌሎች ወንጀሎች በተለዬ የፈረንሳይ ሕግ ወሲባዊ ወንጀሎችን ለመቆጣጠርና ለመቅጣት የሰጠውን ትኩረት የሚያመላክት ሊሆን ይችላል።

ምንም እንኳ በጥቅሉ በስካር ወይም በሌሎች አደንዛዥ ነገሮች የአዕምሮው የማመዛዘን አቅም በተዳከመበት ወይም በጠፋበት ወንጀል የፈጸመ ሰው ኃላፊነት ባይኖርበትም በብዙ አገራት ሕግጋት ውስጥ ወንጀሉን የፈጸመው ሰው የሰከረው ወንጀል ለመፈጸም አስቦ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጉዳይ መሠረታዊ ነጥብ ነው። ለምሳሌ፦ በአሜሪካ ሕግ በስካር አንድ ወንጀል የፈጸመ ሰው ከኃላፊነት ነጻ የሚሆነው ወንጀል ለመፈጸም አስቦ ስካር ውስጥ እስካልገባ ድረስ ነው።[14] በተወሰኑ የአሜሪካ ግዛቶች ፍርድ ቤቶች ወንጀል ለመፈጸም በነጻ ፈቃድ መስከር (voluntary intoxication) ከኃላፊነት ነጻ ለመሆን እንደ መከራከሪያ ቢቀርብም ተቀባይት የለውም፤ መከራከሪው ክስ የሚመሠረትበትን ወንጀል ደረጃ ዝቅ ለማድረግና ቅጣትን ለማቅለል ብቻ ጥቅም ላይ ይውላል።[15] በመሆኑም ሕጉ በስካር ለተፈጸመ ወንጀል ከኃላፊነት ነጻ ለመሆን ወንጀል ለመፈጸም አስቦ በነጻ ፈቃድ በመስከርና ካለፈቃድ ሰክሮ (involuntary intoxication) ወንጀል በመፈጸም መካከል ልዩነት ማስቀመጡን እንገነዘባለን። የእንግሊዝ ሕግም በተመሳሳይ መልኩ በነጻ ፈቃድ በመስከርና ካለፈቃድ በመስከር መካከል ልዩነት የሚያስቀምጥ ሲሆን ወንጀሉን የፈጸመው ሰው ካለፈቃዱ የሰከረ ከሆነ ከወንጀል ኃፊነት ነጻ ይሆናል።[16]

## 2. ጥፋትን ማመን እንዲሁም በቁሳዊ ችግር የተፈጸመ ወንጀል ከኃላፊነት ነጻ በማድረግ ወይም ቅጣትን በማቅለል ረገድ ያላቸው አስተዋጾ

### 2.1. ጥፋትን ማመን

ተከሳሾች በተከሰሱበት ወንጀል ላይ በተለያየ መልኩ ለፍትሕ አካላት ለሚያደርጉት ትብብር የሚጣልባቸውን መደበኛ ቅጣት መቀነስ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ አገራት የወንጀል ሕግ ውስጥ ሲሠራበት የቆየ ነው። በተመሳሳይ መልኩ የተከሰሱበትን ወንጀል ያመኑ ተከሳሾችን ከሌሎቹ ጥፋታቸውን ካላመኑት ጋር ሲነጻጸር አነስተኛ ቅጣት መቅጣት የተለመደ ነው።[17]

የጉዳዩን ታሪካዊ አመጣጥ በአጭሩ ለመዳሰስ በመጀመሪያ የኮመን ሎው የሕግ ሥርዓትን እንመልከት። ጥፋትን ማመን በኮመን ሎው የሕግ ሥርዓት ውስጥ የነበረው ቦታና ታሪካዊ አመጣጥ በደንብ ያልተጠና፣ ያልተሰነደና አከራካሪ የሆነ ጉዳይ ነው።[18] ጥፋትን ማመን

---

[13] ዝኒ ከማሁ።

[14] Obi N.I. Ebbe (ed.), Comparative and International Criminal Justice Systems: Policing, Judiciary, and Corrections, (CRC Press, Boca Raton, London, New York, 3rd ed.), 30 (2013).

[15] ዝኒ ከማሁ።

[16] ገብርዔል ሀልቨይ፣ ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 2፣ ገጽ 143።

[17] Douglas Husak, The Philosophy of Criminal Law, Selected Essays, (Oxford University Press, Oxford, New York) 313 (2010).

[18] Joseph B. Sanborn Jr., A Historical Sketch of Plea Bargaining, 3 Just. Q. 111 (1986).

በኮመን ሎው የሕግ ሥርዓት ከመቼ ጀምሮ ነው ሥራ ላይ የዋለው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ሁለት የክርክር መስመሮች ያሉ ሲሆን የመጀመሪያው የክርክር መስመር ጥፋትን ማመን ጥቅም ላይ የዋለው የወንጀል ፍትሕ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ነው የሚል ነው፤[19]ሁለተኛው የክርክር መስመር ጉዳዩን በአንጻሩ የቅርብ ጊዜ ክስተት አድርጎ የሚያቀርብ ሲሆን በዋናነት የ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የአሜሪካ የርስበርስ ጦርነትን መነሻ ያደርጋል፡፡[20] ይህንን የ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ለአሜሪከ ብቻ ሳይሆን በእንግሊዝም የጉዳዩ መነሻ ጊዜ አድርገው የሚቆጥሩ ጸሕፍት አሉ፡፡[21] እነዚህን ሁለት ጽንፎች ለማስታረቅ የሚቀርበው ሦስተኛው አመራጭ ሃሳብ የጉዳዩን አጀማመርና ታሪካዊ አመጣጥ ከአሜሪካ የርስበርስ ጦርነት በፊት እንደነበር ያስቀምጣል፡፡[22]

ጥፋትን ማመን የአኅጉረ አውሮፓ የሲቪል ሎው ሕግ ሥርዓት በሚከተሉ አገራት ዘንድ የነበረውን ታሪካዊ ቦታ ስንመለከት ከዚህ በላይ ከተመለከትነው የኮመን ሎው የሕግ ሥርዓትን ከሚከተሉ አገራት የተለዩ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ጥፋትን ማመን የአኅጉረ አውሮፓ የሲቪል ሎው ሕግ ሥርዓት ውስጥ በአንጻሩ የቅርብ ጊዜ ክስተት ሲሆን ጠንካራ ታሪካዊ መሠረት አልነበረውም፡፡ ለዚህ በዋናነት እንደ ምክንያት የሚጠቀሰው በእነዚህ ሁለት የሕግ ሥርዓቶች ውስጥ የወንጀል ክርክር ሂደቱ የሚመራበት መሠረታዊ ልዩነት በመኖሩ ነው፡፡ በኮመን ሎው የሕግ ሥርዓት በወንጀል ክርክር ሂደት እውነቱን የማሳየት ሸክም የተከራካሪ ወገኖች (adversarial) በመሆኑ የፍርድ ቤቶች ሚና ውስን ነው፡፡ በተቃራኒው የአኅጉረ አውሮፓ የሲቪል ሎው ሕግ ሥርዓትን በሚከተሉ አገራት ዘንድ በወንጀል ክርክር ሂደት እውነቱን በማረጋገጥ ሂደት ውስጥ ፍርድ ቤቶች (inquisitorial በመሆኑ)ጉልህ ሚና ይጫወታሉ፡፡ በመሆኑም በኮመን ሎው የሕግ ሥርዓት ውስጥ ተከሳሹ ጥፋቱን አምኖ ከሳሹ አቃቤ ሕግ የሚጣለውን ቅጣት አቅልሎ ካቀረበ ከፍርድ ቤቶች የሚጠበቀው ሚና ይህንን የሁለቱን የከሳሽና የተከሳሽ ስምምነት ከማጽደቅ ብዙም የዘለለ አይደለም፡፡[23] በተቃራኒው የአኅጉረ አውሮፓ የሲቪል ሎው ሕግ ሥርዓት በሚከተሉ አገራት ዘንድ ግን የፍርድ ቤቶች ሚና ከዚህ የዘለለና እውነትን ከመፈለግ ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው፡፡[24] ነገር ግን ምንም አንኳ የአኅጉረ አውሮፓ የሲቪል ሎው ሕግ ሥርዓት በባሕርይው ጥፋትን ከማመንና ይህንን ተከትሎ ቅጣትን ለማቅለል ከአቃቤ ሕግ ጋር ከሚደረገው ስምምነትና በጉዳዩ ለይ ፍርድ ቤቶች ከሚኖራቸው ሚና ጋር የማይጣጣም ቢሆንም በሕግ ሥርዓቱ ውስጥ ያሉ አገራት ይህንን አሠራር የሕጋቸው አካል ለማድረግ ፍላጎት እያሳዩ መጥተዋል፡፡[25] ለዚህ መሠረታዊ ለውጥ በምክንያትነት የሚጠቀሰው በእነዚህ አገራት የወንጀል ቁጥር በመበራከቱና ይህንን ተከትሎ ከዚህ ቀደም ሲሠራበት በነበረው በነባሩ

[19] Alschuler, A. W., Plea bargaining and its history, 13(2) Law & Soc'y Rev. 212 (1979).
[20] ጆሴፍ ቢ. ሳንቦርንጂአር፣ ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 18፣ ገጽ 112፡፡
[21] John H. Langbein, Understanding the Short History of Plea Bargaining, 13 LAW & Soc'y REV. 261 (1979).
[22] ጆሴፍ ቢ. ሳንቦርንጂአር፣ ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 18፣ ገጽ 113፡፡
[23] Maximo Langer, From Legal Transplants to Legal Translations: The Globalization of Plea Bargaining and the Americanization Thesis in Criminal Procedure, 45 HARV. INT'l L.J. 1 36 (2004).
[24] ዝኒ ከማሁ፣ገጽ 37፡፡
[25] ዝኒ ከማሁ፡፡

የወንጀል ፍትሕ ሥነ-ሥርዓት አማካይነት እየተበራከተ ለመጣው ወንጀል በአጭር ጊዜ እልባት መስጠት አስቸጋሪ በመሆኑ ነው፡፡[26]

በአሁኑ ወቅት በተለይ የኮመን ሎው የሕግ ሥርዓት በሚከተሉ ብዙ አገራት የተከሰሱበትን ወንጀል በማመን ቅጣትን መቀነስ እየተለመደ የመጣ አሠራር ነው፡፡[27] ነገር ግን ይህንን ጉዳይ ከክፊል ይቅርታ ጋር መዛመድ አለመዛመዱን በንድፈ-ሃሳብ ደረጃ ያቀረቡና የተነተኑ የዘርፉ ሊቃውንት አልተገኙም፡፡[28] በመሆኑም የተከሰሱበትን ወንጀል ማመንና ይህን ተከትሎ ቅጣትን ከማቅለል ጀርባ ሊኖር የሚችለው ምክንያት ተከሳሹ የአቃቤ ሕግንና የፍርድ ቤቶችን ጊዜ በመቆጠቡ ይህም ለፍትሕ አስተዳደር ሥርዓቱ መሳለጥ አስተዋጾ በማድረጉ ነው ብሎ መገመት ይቻላል፡፡[29] ይህ ጥፋትን ከማመን ጀርባ ያለውን ምክንያት እ.አ.አ. በ2007 ተሻሽሎ የወጣው የእንግሊዝ የቅጣት ማቅለያ መመሪያ በግልጽ አስቀምጦታል፡፡[30] በተግባር እንደሚታየውና በሌሎች አገሮች የፍርድ ቤት ውሳኔ ላይም እንደሚንጸባረቀው የተከሰሰበትን ወንጀል ማመኑ ብዙውን ጊዜ ተከሳሹ በፈጸመው ወንጀል ተጸጽቷል የሚል ምክንያት ይሰጠዋል፡፡[31]

### 2.2. በአስገዳጅ ሁኔታ የተፈጸመ ወንጀል

በተለያዩ አገራት የወንጀል ሕጎች ሰዎች ከአቅም በላይ የሆነ ችግር (necessity) ገጥሟቸው ለሚፈጽሙት በሕግ የተከለከሉ ተግባራት ወይም ወንጀል ከኃላፊነት ነጻ ማድረግ ከብዙ ዘመናት ጀምሮ እውቅና ያገኘ ጉዳይ ነው፡፡ እነዚህ ከአቅም በላይ የሆኑ ችግሮች የተለያዩ ሲሆኑ የሰው እጅ የሌለበትና በተፈጥሮ የሚከሰቱ ችግሮችን (Act of God) እንዲሁም ሊቀለበሱ የማይችሉ ድንገተኛ አደጋዎችን ይጨምራሉ፡፡ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ትርጓሜና ይዘት ለማስረዳት ብዙ ጸሕፍት የ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንግሊዛዊ የሕግ ብሂል (legal maxim) ፀሀፊ የነበሩትን ሰር ፍራንሲስ ባኮንን በዋቢነት ይጠቅሳሉ፡፡ ባኮን ከአቅም በላይ የሆነ ችግርን በሦስት የከፈሉት ሲሆን አንዱ የራስን ሕይወት ማዳን (conservation of life (self preservation)) ነው በማለት ይጠቅሳሉ፡፡[32] ሕይወትን ማዳን

---

[26] ዝኒ ከማሁ፡፡

[27] Geraldine MacKenzie, The Guilty Plea Discount: Does Pragmatism Win over Proportionality and Principle, 11 S. Cross U. L. Rev. 206 (2007).

[28] ዳግላስ ሁሳክ፣ ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 17፣ ገጽ 313፡፡

[29] ዝኒ ከማሁ፡፡ ዳግላስ ሁሳክ፣ ከዚህ በላይ ማስወሻ ቁጥር 17 Andrew Ashwoorth, Sentencing and Criminal Justice, (Butterworths, London, 2nd ed., London), 137 (1995) ጠቅሰው እንደጻፉት፡፡

[30] *A reduction in sentence is appropriate because a guilty plea avoids the need for a trial (thus enabling other cases to be disposed of more expeditiously), shortens the gap between charge and sentence, saves considerable cost, and, in the case of an early plea, saves victims and witnesses from the concern about having to give evidence. The reduction principle derives from the need for the effective administration of justice and not as an aspect of mitigation.* (SGS, Reductioin in Sentence for a Guilt Plea, Revised Guideline, para. 2.2, (2007)

[31] Andrew Ashwoorth, Sentencing and Criminal Justice, (Cambridge, London, 6th ed., London), 181 (2015).

[32] John C. Hogan & Mortimer D. Schwartz, On Bacon's Rules and Maxims of the Common Law, 76 Law. Libr. J. 72 (1983).

ምን ማለት እንደሆነ ባኮን ሲያብራሩ "አንድ ሰው ርቦት ጊዜያዊ ርሃቡን ለማስታገስ ምግብ ቢሰርቅ የስርቆት ወንጀል አልፈጸመም" በማለት ይገልጻሉ።[33]

ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ትርጓሜን በዚህ መልኩ ማስቀመጥ ቢቻልም አከራካሪው ጉዳይ ግን በተግባር ምን ምን ጉዳዮች ከወንጀል ኃላፊነት ነጻ ለመሆን በሕግ ተደንግገው እንደመከራከሪያነት ያገለግላሉ የሚለው ጥያቄ በአጭሩና በቀላሉ የሚመለስ አይደለም። በተለይ በዚህ ንዑስ ክፍል ሥር የምንዳስሰው በቁሳዊ ችግር የተፈጸመ ወንጀልን በተመለከተ የተለያዩ አገራት ሕግጋት ምን ይላሉ የሚለው ጥያቄ መሠረታዊ ጥያቄ ሲሆን ሕግጋቱ ጉዳዩን በተለያየ መልኩ ደንግገውት እናገኛለን።

ጉዳዩ በአሜሪካ ሕግ ውስጥ ያለውን ቦታ ለመረዳት ቀደምት የፍርድ ቤት ውሳኔዎችን ስንመለከት ርሃብን በመሳሰሉ ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ሳቢያ ተገፋፍቶ ወንጀል መፈጸም ቅጣትን ለማቅለል እንጂ ከወንጀል ኃፊነት ነጻ ለመሆን በመከራከሪያነት አይቀርብም ነበር።[34] ጉዳዩን ለማብራራት እ.አ.አ በ1933 ለፍርድ ቤት የቀረበ ጉዳይ (State v. Moe) እንመልከት። በዋሽንግተን ግዛት ነዋሪ የሆኑ ሥራ አጥ ሰዎች የምግብ ገበያ ማዕከል በመውረር ለተከሰሱበት የስርቆት ወንጀል ድርጊቱን የፈጸምነው ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ስለገጠመን ነው የሚል መከራከሪያ ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ ኢኮኖሚያዊ ችግር ለወንጀል ክስ መከላከያ ሆኖ መቅረብ አይችልም፤ ችግሩ ነበር ቢባል እንኳ ይህንን መቀበል ግለሰቦች ሕጉን በእጃቸው እንዲያስፈጸሙት መፍቀድ ይሆናል፤ የሚል ምላሽ በመስጠት መከራከሪያውን ውድቅ አድርጎታል።[35]

ቀደምት የእንግሊዝ ፍርድ ቤት ውሳኔዎችን ስንመለከት ጉዳዩ በአሜሪካ ሕግ ከተሰጠው ቦታ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ፋና ወጊ ከሆኑ ውሳኔዎች ውስጥ ተጠቃሽ የሆነውን The Queen v. Dudley and Stephens በአጭሩ እንመልከት። ክሱ የቀረበው እ.አ.አ. በ1884 ሲሆን ዳድሊና ስቲፈንስ የተከሰሱበት ወንጀል ባሕር ላይ ለሃያ ቀናት ምግብና ውሃ በማጣታቸው በነበሩበት መርከብ ላይ የሚሰራ ፓርከር የተባለ ባልደረባቸውን በመግደል ብሩክስ ከተባለና በድርጊቱ ካልተስማማ ጓደኛቸው ጋር በልተዋል የሚል የግድያ ወንጀል ነው።[36] ተከሳሾች ያቀረቡት መከራከሪያ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ወይም ጽኑ ረሃብ ሲሆን ፍርድ ቤቱ መከራከሪያውን ውድቅ በማድረግ በተከሳሾች ላይ የሞት ቅጣት ወስኗል።[37]

ወደ አሜሪካ ሕግ ተመልሰን በጊዜ ሂደት ለጉዳዩ የተሰጠውን የሕግ ምላሽ እንመልከት። በአሜሪካ የሕግ ኢንስትቲዩት እ.አ.አ. በ1962 ተረቅቆ የወጣው የአሜሪካ ሞዴል የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ከዚህ በላይ ከተሰጡ የፍርድ ቤት ውሳኔዎች ለየት ያለና "በእኩዮች ምርጫ"

---

[33] ዝኒ ከማሁ፣ገጽ 73። ባኮን ርሃብን ተከትሎ ከሚፈጸም ስርቆት በተጨማሪ ጉዳዩን የባሕር ጠላቂዎች ሊገጥማቸው ከሚችል ድንገተኛ አደጋና ሕይዎታቸውን ለማዳን ከሚያደርጉት ጥረት ጋር በማገናኘት ጉዳዩን እንደሚከተለው ያብራራሉ፦ "So if divers bee in danger of drowning by the casting away of some boate or barge, and one of them get to some plancke, or on the boates side to keep himself above water, and another to save his life thrust him from it, whereby hee is drowned; this is neither *se defendendo* nor by misadventure, but justifiable."

[34] George W. III Hersey & Alfred Avins, Compulsion as a Defense to Criminal Prosecution, 11 Okla. L. Rev. 292 (1958).

[35] Michele Cotton, The Necessity Defense and the Moral Limits of Law, 18 New Crim. L. Rev. 41 (2015).

[36] Queen's Bench Division 14 Q.B.D. 273 (1884).

[37] ዝኒ ከማሁ።

መርኅ ላይ የተመሠረተ ድንጋጌ አውጥቷል፡፡[38] በዚህ ሕግ መሠረት የአንድ ሰው ድርጊት ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ሆኖ የሚቆጠረው በራሱ ላይ ወይም በሌሎች ሰዎች ላይ የተጋረጠን ጉዳት ወይም እኩይ ተግባር ለመቀልበስ የተከናወነ እና የተቀለበሰው ጉዳት ወይም እኩይ ተግባር በሕግ ጥበቃ ከተሰጠው መብት በልጦ ሲገኝ ነው፡፡[39] ይህ ሞዴል የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ድንጋጌ ከተለመደውና አሪታዊ ከሆነው "ከአቅም በላይ የሆነ ችግር" ምንነትና አረዳድ ላይ የተመሠረተ አይደለም፡፡[40] ምንም እንኳ ሞዴል የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ይህንን በመስፈርት ላይ የተመሠረተ ድንጋጌ ቢያስቀምጥም ከተወሰኑ ግዛቶች በስተቀር የፌደራል መንግሥቱም ሆነ አብዛኞቹ ግዛቶች ይህንን ሕግ ሙሉ በሙሉ ወስደው የሕጋቸው አካል አድርገው አልተቀበሉትም፡፡[41]

ከዚህ በላይ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር የኮመን ሎው የሕግ ሥርዓት በሚከተሉት አሜሪካና እንግሊዝ ምን እደሚመስል ተመልክተናል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ጉዳዩ በአኅጉረ አውሮፓ የሲቪል ሎው የሕግ ሥርዓት ምን እንደሚመስል በአጭሩ እንዳስሳለን፡፡ ከአሜሪካና ከእንግሊዝ ሕግጋት በተቃራኒው በአኅጉረ አውሮፓ የሲቪል ሎው የሕግ ሥርዓት ውስጥ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ከወንጀል ኃላፊነት ነጻ ለመሆን በመከራከሪያት ሲያገለግል ቆይቷል፤ በምሳሌነት እ.አ.አ. በ1871 የወጣውን የጀርመን የወንጀል ሕግና እ.አ.አ. በ1810 የወጣውን የፈረንሳይ ሕግ መጥቀስ ይቻላል፡፡[42] ከዚህ ጉዳይ ጋር በተለይም ርሀብን ለስርቆት ወንጀል ክስ እንደመከላከያ ከማቅረብ ጋር በተያያዘ በብዙ ጸሐፍት የሚጠቀስ የፈረንሳይ ፍርድ ቤት ውሳኔ አለ፡፡ ክሱ የቀረበው እ.አ.አ. በ1898 ሲሆን መደበኛ ሥራ ማግኘት ባልቻለች ሊዊ ሜና በተባለች ከእናቷና ወታደራዊ አገልግሎት በመስጠት ላይ ከሚገኝ እጮኛዋ ከወለደችው ሕጻን ልጇ ጋር የምትኖር የሃያ ሁለት አመት ወጣት ላይ የቀረበ ነው፡፡[43] ሜና፣ እናቷና ሕጻን ልጇ ለሰላሳ ስድስት ሰዓታት የሚላስ የሚቀመስ አጥተው ከቆዩ በኋላ ዳቦ በመስረቋ ተከሳ ታሰረች፡፡ ጉዳዩ የቀረበላቸው ማኒው የተባሉ የችሎቱ ሰብሳቢ ዳኛ በወቅቱ ስርቆትን ይቀጣ የነበረውን ሕግ ወደ ጎን በመተው የሚከተለውን ወስነዋል፦ "በዚህ በደንብ በተደራጀ ማኅበረሰብ ውስጥ አንድ የማኅበረሰቡ አባል በተለይም እናት ካለጥፋቷ ዳቦ ማጣቷ ያጸጽታል፤ አንድ ሰው መሠረታዊ ፍላጎቱ የሆነውን ዳቦ ለማግኘት ተገፋፍቶ ድርጊቱን መፈጸሙ ይህን ተራና ከወቀሳ የማያልፍ ተግባር የወንጀል ተፈጥሮውን እንዲያጣ ያደርገዋል፡፡"

በአሁኑ ውቅት በፈረንሳይ ሕግ ውስጥ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ለሁሉም አይነት ወንጀሎች እንደ መከላከያ የሚያገለግል ሲሆን ለዚህም ሦስት ቅድመ-ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፤ እነሱም በቅርብ የተጋረጠ አደጋ መኖር፣ ይህ አደጋ ለወንጀሉ መፈጸም ምክንያት መሆን ይኖርበታል፣ እንዲሁም የተፈጸመው ወንጀል ከተጋረጠው አደጋ ጋር

[38] ሚሽል ኮተን፣ ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 35፣ ገጽ 42፡፡
[39] The Model Penal Code, § 3.02 (1962).
[40] ሚሽል ኮተን፣ ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 35፣ ገጽ 42፡፡
[41] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 42-43፡፡
[42] George P. Fletcher, Rethinking Criminal Law, (Oxford University Press, New York), (2000).
[43] ከዚህ በታች ያለው የጉዳዩ ታሪክ የተወሰደው Rachel G. Fuchs, Contested Patrinity, Constructing Families in Moderen France, (The Johns Hopkins Universty Press, Baltimore), 98 (2008) ላይ ነው፡፡

ተመጣጣኝ መሆን አለበት፡፡ እነዚህ ቅድመ-ሁኔታዎች ከሞላ ጎደል ከዚህ በላይ ከተመለከትነው የአሜሪካ ሞዴል የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ጋር ተመሳሳይ ናቸው፡፡[44]

## 3. የነገሥታት ፍርዶች

### 3.1. በስካር ሁኔታ የተፈጸሙ ወንጀሎች

በስካር ከተፈጸመ ወንጀል ጋር የተያያዘ የመጀመሪያው ፍርድ የተሰጠው በዐፄ ኢያሱ በሥመ-መንግሥታቸው አድያም ሰገድ ነው፡፡ ዐፄ ኢያሱ ከ1674-1694 ዓ.ም ድረስ በድምሩ ለሃያ አራት ዓመታት ኢትዮጵያን ያስተዳደሩ ንጉሥ ናቸው፡፡ ለፍርዱ መነሻ የሆነው ጉዳይ የሚከተለው ነው፦

> ከዕለታት አንድ ቀን በጥቂት የእልፍኝ አሽከሮቻቻው ታጅበው ጎንባሲት በምትባለው በር ወጥተው ፈረሳቸው በወርቅ መጣብር አጊጦ ባማረ የወርቅ እቃ ተጭኖ እፊታቸው እየተሳበ ሲሄድ አንድ መጠጥ ያሸነፈው ሰው እመንገድ አገኛቸውና ይህ ፈረስ ይሸጣልን ብሎ ጠየቃቸውና አለፈ፡፡ ንጉሡም በትዕግሥት ከኋላው ተከትላችሁ የሚገባበትን ቤቱን እዩ ብለው ስላዛዙ የታዘዘው አሽከር በመጠጥ የተሸነፈው ሰውየ የገባበትን ቤት አይቶ ተመለሰ፡፡ በማግስቱ ልብሰ መንግሥታቸውን ለብሰው ግሩማን (ገ፫ርጋዶች) የሆኑትን ጋሻ ጃግሬዎቻቸውን ግራና ቀኝ አቁመው እችሎት ተቀመጡ፡፡ ከዚህ በኋላ ያንን ሰው አስጠርተው ያንኑ ፈረስ ቀድሞ ተጭኖ የነበረውን የወርቅ ዕቃ እንደተጫነ እመካከል አስቁመው ያውልኽ ትላንት ልትገዛው ጠይቀኽ የነበረውን ፈረስ አሁን ግዛው አሉት፡፡ ይኽንንም ማለታቸው ግዥውን እንደትላንትናው በድፍረት የገፋበት እንደሆነ ወይም መልስ ያጣ እደሆነ ለመቅጣት ይመስላል፡፡[45] ነገር ግን ሰውየው ጮሌ የነገር መላ አዋቂ ኖሮ ትላንት ከኔ ጋራ ከነበሩት ባልንጀሮቼ መክሬ ነው የምገዛው ሲል መለሰ፡፡
>
> ንጉሡም "ትላንት ስናይህ ብቻህን አልነበርህምና ምን ባልጀራ ነበረኽ" ቢሉት "ትላንትና የነበሩት ባልንጀሮች ከጠላና ከጠጅ የሚገቡት ሥሮች እነጌሾ እነግራዋ እነብቅል ናቸው" ብሎ መለሰላቸው፡፡ ንጉሡም የንግግሩ አካሄድ ስላሳቃቸው[46] ቁጣቸውን ወደ ምሕረት መልሰው በሠላም ወደ ቤቱ እንዲሄድ አሰናበቱት ይባላል፡፡[47]

ከስካር ጋር የተያያዘ ሁለተኛው ፍርድ የተሰጠው በዐፄ ዳዊት ሣልሳዊ በሥመ-መንግሥታቸው አድባር ሰገድ ነው፡፡ ዐፄ ዳዊት ኢትዮጵያን ከ1708-1713 ዓ.ም ድረስ ያስተዳደሩ ንጉሥ ሲሆኑ የዐፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ልጅ ናቸው፡፡ አንባቢ ጉዳዩን በሚገባ እንዲረዳው የጉዳዩ አመጣጥና የንጉሡ ፍርድ እንዲሚከተለው በዝርዝር ይቀርባል፦

> ደግሞ ከእለታት አንድ ቀን የሰው ገንዘብ ሳይደባልቅ ደክሞ ባፈራው ገንዘብ የሚኖር ማነው ብለው ጠየቁ፤ባጠገባቸው ያሉ ባለሟሎች ገበሬ ነው ብለው

---

[44] Catherine Elliot, French Criminal Law, (Routledge Taylor and Francis Group, London, New York, 1st ed.), 114 (2001).

[45] ይህ ድርጊት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 607ና ተከታዮቹ ሥር በተደነገገው መሠረት በክብር ላይ የተፈጸመ ወንጀል ነው ሊባል ይችላል፤ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ፣አዋጅ ቁጥር 414/1997፣ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ ልዩ እትም፣ አንቀጽ 607ና ተከታዮቹ፡፡

[46] "ንጉሡም የንግግሩ አካሄድ ስላሳቃቸው ቁጣቸውን ወደ ምሕረት መልሰው በሠላም ወደ ቤቱ እንዲሄድ አሰናበቱት" የሚለው አገላለጽ ጉዳዩ በታየበት ችሎት በአጋጣሚ (incidentally) የተከሰቱ ክስተቶችን ለማመላከት የገባ እንጂ የውሳኔው መነሻ ተከሳሹ ሰክሮ ድርጊቱን መፈጸሙ ሳይሆን በፍርድ ሂደቱ የተናገረው ነገር ንጉሡን ስላሳቃቸው ነው፤ የሚል መደምደሚያ ላይ ለመድረስ አለመሆኑን አንባቢ ልብ ሊለው ይገባል፡፡

[47] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵ ታሪክ፣ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ*፣ (ትንሣኤ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ)፣ 304(1953)፡፡

> መለሱላቸው፤ንጉሡም ገበሬዎቹ ውስጥ ሽማግሎዎች የሆኑትን መርጣችሁ አምጡልኝ ብለው አመጡላቸውና ከነሱ ጋር እሁድ እሁድ ሰንበቴ አብረው ይጠጡ ጀመር።
>
> ከሰንበታቶቹ በአንደኛው ቀን ትኵስ ወተት የሚመስል ቡሌ የሚባለውን ኃይለኛ የጎንደር ጠላ ደጋግሞ ጠጥቶ በዚሁ መጠጥ አእምሮው የተነካ አንድ ማኅበርተኛ ተነስቶ ንጉሱን በጥፊ መታቸው። ሰውም እንምታው እያለ ሲጋበዝ ርሳቸው መጠጥ ቢያሸንፈው ነውና ተውት ይልቅስ እቤቱ ወስዳችሁ አስተኙት ብለው አዘዙና ወስደው አስተኙት።
>
> በማግስቱ ችሎት ተዘርግቶ በዚህ ሰውየ ላይ ፍርድ ተጀመረ። መኳንንቱም ሊቃውንቱም የሞት ፍርድ ፈረዱበት። እንዲሁም አራቱ ሊቀ መጣኞች አዛዦች[48] (ባለፍትሐ ነገሥቶች) "ዘያወርድ እዴሁ ዲበ መሲሐ እግዚአብሄር ይትመተር እዴሁ (እግዚአብሄር ቀብቶ ባነገሠው ላይ እጁን የሚዘረጋ እጁ ይቆረጥ)" የሚለውን ጠቅሰው የሞት ፍርድ ፈረዱበት።
>
> ንጉሡም ይኸን ሁሉ ከሰሙ በኋላ ከችሎት እልፍኛቸው ተመልሰው ገቡ። በዚያውም ሊቃውንቱንና መኳንንቱን ወንጀለኛውም ጭምር አስጠርተው በነሱ ፊት አንድ የአንበሳ ለማዳና የዝንጀሮ ለማዳ አስመጥተው አቆሙ። ዝንጀሮውም አንበሳውን አይቶ በፍርሀት ይንቀጠቀጥ ጀመር። በኋላ ግን በቆሬ[49] ሙሉ ጠጅ አቀረቡላቸው ሁለቱም አብረው ጠጡ። ከዚህ በኋላ ዝንጀሮው ፍርሀቱ ተወገደለትና እንደልቡ ይቀናጣ ጀመር፤ እንዲያውም በአንበሳው ራስ ላይ ወጥቶ እየተዝናና ተቀመጠ።
>
> በዚህ ጊዜ ፊታቸውን ወደ መኳንንቱ አዙረው አሁንስ በማን ትፈርዳላችሁ ቀድሞውንም ከገበሬ ጋር ማኅበር በመጠጣቱ ያጠፋሁ እኔ ነኝ በማኅበርና በቦታ ባንገናኝ ኖሮ ይህ ሰው መቼ ይደፍረኝ ነበር ብለው ወደ ችሎት ተመልሰው ምሕረት አድርገው ወደ ቤቱ በሠላም ሰደዱት ይባላል።[50]

እነዚህ ከዚህ በላይ የቀረቡት ሁለት ጉዳዮች ምንም እንኳ በተለያየ ጊዜ የተፈጸሙና በሁለት ነገሥታት ፍርድ የተሰጠባቸው ቢሆኑም አንድ የሕግ ጭብጥ ያመሳስላቸዋል፤ ወንጀሎቹ በተፈጸሙበት ከዛሬ ሦስት መቶ ዓመታት በፊት በነበረው ዘመን እሳቤና ሕግ መሠረት በስካር የተፈጸመ ወንጀል ኃላፊነትን እንደማያስከትል የሚያሳዩ ናቸው። በተለይ ዐፄ ዳዊት ጉዳዩን የዱር እንስሳትን በመጠቀም ድራማዊ በሆነ መልኩ ለመኳንንቱና ሊቃውንቱ ማቅረባቸው ስካር ወይም የአልኮል መጠጥ የሚያስብ አዕምሮ ባለቤት የሆነውን የሰው ልጅ ብቻ ሳይሆን በደመ-ነፍስ (instinctively) የሚንቀሳቀሱ እንስሳትን ባሕርይ ጭምር ሙሉ በሙሉ እንደሚቀይር ለማስረዳት የሄዱበት ርቀት አቻ የማይገኝለት ዘዴ ሲሆን እግረ መንገዱን የንጉሡን ጥበብ የተሞላበት ዳኝነት (judicial wisdom) በደንብ የሚያሳይ ነው።[51]

---

[48] ሊቀ መጣኝ አዛዥ ማለት የፍርድ ቤት ዳኛ ማለት ነው። ሊቀ መጣኞች ለዳኝነት ሥራ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ተግባራት ሹመትን ጨምሮ ነገሥታትን ያገለግሉና ያግዙ ነበር። ቁጥራቸው ሁለት በሆነ ጊዜ አንዱ ሊቀ መጣኝ ከንጉሡ በስተግራ ሌላው በስተቀኝ ይቀመጣሉ። ከዚህ በላይ በቀረበው ጉዳይ ላይ ሊቀ መጣኝ አዛገሮች የፍትሐ ነገሥት ሊቃውንት ሲሆኑ ቁጥራቸው አራት ስለሆነ ሁለቱ ሊቀ መጣኞች ከንጉሡ በስተግራ ሁለቱ ከንጉሡ በስተቀኝ ይቀመጣሉ። ይህንን ከንጉሡ አኳያ ያላቸውን የአቀማመጥ ሥርዓት ተከትሎ ሊቀ መጣኝ አዛገሮች የቀኝ አዛዥና የግራ አዛዥ የሚል ማዕረግ የሚሰጣቸው ሲሆን የቀኝ አዛዥነት ከግራ አዛዥነት የበለጠ ማዕረግ ነበር። የሊቀ መጣኝ አዛዥን ትርጉምና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን የበለጠ ለመረዳት Bairu Tafla and Heinrich Scholler, SER'ATA MANGEST: An Early Ethiopian Constitution, Verfassung und Recht in Übersee / Law and Politics in Africa, Asia and Latin America, Vol. 9, No. 4, 487-499(1976) ይመለከቷል።

[49] ቆሬ ማለት እንደዋንዛ ካለ ግንድ እየተጠረበ የሚሰራና ለውሃ መያዣ፣ ለማስታጠቢያ የሚያገለግል የቤት ዕቃ፣ ገበቴ ማለት ነው (አማርኛ መዝገበ ቃላት፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር የተዘጋጀ፣ ገጽ 208)።

[50] ተክለ ጻድቅ መኵሪያ፣ ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 47፣ ገጽ 335-36።

[51] ምንም እንኳ ንጉሡ "ቀድሞውንም ከገበሬ ጋር ማኅበር በመጠጣቱ ያጠፋሁ እኔ ነኝ" ማለታቸው የፍርድ ጥበባቸውን አያሳይም፤ በተቃራኒው ለገበሬ ያላቸውን ንቀት ያሳያል፤ ሰውዬው ወንጀሉን የፈጸመው ስለጠጣ እንጂ

በስካር ማለትም በአልኮል መጠጥ ወይም አእምሮን በሚያደነዝዝ ነገር የተፈጸም ወንጀል ኃላፊነት እንደማያስከትል በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ ተደንግጎ ይገኛል፡፡[52] በወንጀል ሕጉ በስካር፣ በአልኮል መጠጥ ወይም አእምሮን በሚያደነዝዝ ነገር የተፈጸም ወንጀል ከኃላፊነት ነጻ የሚያደርገው ወንጀለኛው ወንጀል ለመፈጸም በማቀድ ወይም ሊፈጽም እንደሚችል እያወቀ ራሱን ለስካር (አእምሮን ለሚያደነዝዝ ነገር) ያላጋለጠ ከሆነ ነው፡፡[53] ከዚህ ቀደም ሲል እንደተመለከትነው የኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ እንደ አሜሪካ ሕግ አስቦ በነጻ ፈቃድ በመስከርና ካለፈቃድ ሰክሮ ወንጀል በመፈጸም መካከል ልዩነት ያስቀመጠ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

ምንም እንኳ ከዚህ በላይ የቀረቡ ሁለት ጉዳዮችን ባያጠቃልልም በስካር የተፈጸመ የግድያ ወንጀል ከኃላፊነት ነጻ እንደሚያደርግ፣ በተለይም በዘመኑ የነበረው "የገደለ ይሙት" የሚለው ፍርድ እንደማይፈጸምበት በጊዜው ሥራ ላይ በነበረው ፍትሐ ነገሥት ውስጥ እንደሚከተለው በግልጽ ተደንግጎ እናገኘዋለን፦

> መግደልም በሁለት ክፍል ይከፈላል ከእነርሱም አንዱ ቅጣት የማይገባው (የማያስቀጣ) ነው፡፡ ይኸውም አዕምሮ የሌለው ነው፡፡ ዘመኑም ከሰባት ዓመት ላልበዛ <u>ለሰካራምም ፍርዱ አዕምሮ እንደሌለው ሰው ስለሆነ ሞት አይገባውም</u>፡፡ <u>ርሱ በፈቃዱ አዕምሮውን አጥፍቷልና</u>፡፡ ለስድብና ለዝንጉዕ ግን አእምሮአቸው ያለፈቃዳቸው ይጠፋል፡፡ ቅጣቱም እንደቅጣታቸው አይሁን፡፡ እርሱ በስካር የለመደ እንደሆነ ልብ ይፈርዳል፡፡ በመንደላቀቅ ቢሆን ግን ቅጣቱ እንደቅጣታቸው አይሆንም፡፡ ይልቁንም በመስከሩ አንድ ጊዜ ሁለት ጊዜ ቢገድል ወይም በሚችና በገዳይ ከጥንት ጠብ ቢኖር በመቀማጠል (በመንደላቀቅ) የታወቀ ካልሆነ በመካከላቸውም ጠብ ባይኖር በሰካራሞች ቅጣት ይቀጣ፡፡ ቅጣቱም ያለፈቃዱ እንደገደለ ሰው ቅጣት ይሁን፡፡ (የማስመር አጽንኦት በፀሀፊው የተጨመረበት)[54]

አጥኚው ይህንን የፍትሐ ነገሥት ክፍል መጥቀስ የፈለገበት ምክንያት ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ጉዳዩ ለሁለቱ ነገሥታት ከቀረቡት ጉዳዮች በተለዬ ከግድያ ወንጀል ጋር ቢገናኝም በስካር ለተፈጸመ ወንጀል ወንጀለኛው ለምን ከኃላፊነት ነጻ እንደሚሆን ምክንያቱን (ratioinale) ስለሚያሳይ ነው፡፡ በፍትሐ ነገሥቱ አገላለጽ በአልኮል መጠጥና አዕምሮን በሚያደነዝዝ ነገር ሰክሮ ወንጀል የፈጸመ ሰው አዕምሮ እንደሌለው ሰው ይቆጠራል፡፡ በዚህ ሁኔታ ወንጀል የሚፈጽም ሰው አዕምሮ እንደሌለው ሰው ክፉና ደጉን መመዘንና መመርመር አይችልም፤ የወንጀል ድርጊቱን ውጤት አያውቅም የሚል መሠረታዊ የወንጀል ሕግ ጽንሰ-ሃሳብ የያዘ ነው፡፡

### 3.2. በንዴት፣ በአስገዳጅ ሁኔታ የተፈጸመ ወንጀልና ጥፋትን ማመን

ዐፄ ኢያሱ የተመለከቱት ሁለተኛው ጉዳይ ንብረታቸው በነበረ በግ ላይ የተፈጸመ ስርቆት ሲሆን ጉዳዩ የሚከተውን ይመስል ነበር፦

ገበሬ ስለሆነ አይደለም፤ የሚል ክርክር ማንሳት ቢቻልም ይህ አባባል ድርጊቱ በተፈጸመበት ቅጽበት በንዴትና በጸጸት ንጉሡ የተናገሩት በመሆኑ፣ የንጉሡ ንዴትና ጸጸት በቀል ሆኖ በፍርዳቸው ውስጥ አለመንጸባረቁ እንዲሁም ወንጀሉን የመረመሩበት መንገድ የፍርድ ጥበባቸውን የሚያደበዝዝ አይደለም፡፡

[52] የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ፣ ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 45፣ አንቀጽ 50፡፡

[53] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 50(1)(2)፡፡

[54] ፍትሐ ነገሥት ንባቡና ትርጓሜው፣ (ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት፣ አዲስ አበባ) ፣ 1990፣ አንቀጽ 47፡፡

የድቁስ ቀንድና ቢላዋ ከነማጎደሩ ባንገቱ ያንጠለጠለ የንጉሡ የበግ ሙክት ነበር። እሱም በከተማው እየዞረ የተሰጣውን የመንደር እኽል ይበላ ነበር፤ ሰውም እንዳይመታው የንጉሥ በግ በመሆኑ ይፈራ ነበር። ከእለታት አንድ ቀን አንድ የጎንደር ቁም ፀሀፊ ካህን ቁጭ ብሎ ሲጽፍ ይኸው በግ መጥቶ አጠገቡ ያሰጣውን እኽል በላበት፤ ካህኑም ተነሥቶ ይዞ እቤቱ አርዶ አንገቱ ባለው በራሱ ድቁስ በላው።

ከዚህ በኋላ ካህኑ፦

እድሜ እለምናለሁ ለንጉሥ ኢያሱ፣

ያንን የበግ ሙክት ቢሰደው ንጉሡ፣

በገዛ ቢላዋዉ በገዛ ድቁሱ፣

አመስግኜ በላሁ ከነራስ ምላሱ።

(ማነኽ እንጃልኽ) የሚል ፅፎ በጉፋያ መስጫ ሜዳ ላይ ጥሎት ተገኘ።

ከዚህ በኋላ መጀመሪያ ፅሁፉ ሁለተኛ በብዙ ምርመራ ካህኑ ተገኝቶ ተይዞ እንጉሡ ፊት ቀረበና ይኽን የጻፍክ አንተ አይደለህምን እውነቱን ንገረኝ ብለው ንጉሡ ጠየቁት፤ እሱም እተቀባው ንጉሥ ፊት ቀርቤ ውሸት አልናገርም፤ መችገር ያስደፍራልና ሰው ሁሉ ይህን የንጉሡን በግ ሲፈራ አርጄ የበላሁ ወረቀቱንም የፃፍኩ እኔ ነኝ ሲል በድፍረት ተናገረ፡፡

ንጉሡም በሐቀኝነቱ አመስግነው የገንዘብ ጉርሻ ሰጥተው በሠላም አሰናበቱት ይባላል።[55]

ከተከሳሹ መልስ እንደምንረዳው ወንጀሉን ለመፈጸም የገፋፉት ሁለት ምክንያቶች ሲሆኑ እነሱም ተከሳሹ በመልሱ በግልጽ እንደተናገረው ቁሳዊ እጦትና አንባቢ ከጉዳዩ እንደሚረዳው ወንጀሉን የፈጸመው በንዴት ተነሳስቶ መሆኑ ናቸው። ተከሳሹ "መችገር ያስደፍራል" በማለት የተናገረው ቁሳዊ እጥረት ወይም ረሀብ እንደገጠመው የሚያመላክት ሲሆን የንጉሡ በግ ድርጊት በተከሳሹ ላይ ንዴት እንደፈጠረ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው ተከሳሹ ክሱን በማመኑ ቅጣትን ማቅለል በዘመናዊ የወንጀል ሕግጋት ውስጥ እውቅና ያገኘ ሲሆን በተመሳሳይ መልኩ በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ ቅጣትን ለማቅለል ምክንያቶች ናቸው። በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ ወንጀለኛው ወንጀሉን የፈጸመው ከፍተኛ ቁሳዊ እጦት ደርሶበት ከሆነ፣ የተበደለው ሰው ጠባይ ወንጀለኛውን ብስጭት ላይ ጥሎት እንደሆነ እንዲሁም ወንጀለኛው ተከስሶ ፍርድ ቤት በቀረበ ጊዜ በክስ ማመልከቻው ላይ የተመለከተውን የወንጀል ዝርዝር በሙሉ ካመነ ቅጣት እንደሚቀልለት ተደንግጓል።[56] እነዚህን በሕጉ የተቀመጡ ምክንያቶች ከቀረበው ጉዳይ ጋር ለማነጻጸር ወንጀለኛው በፅህፈት ሥራ የሚተዳደር ባለሙያና ካህን በመሆኑ ከፍተኛ ቁሳዊ እጦት ደርሶበት ነበር፣ በተለይም ርቦት ነበር ለማለት ባያስደፍርም በተወሰነ መልኩ ችግር እንደነበረበት ከሰጠው መልስ መረዳት ይቻላል።[57] በሕጉ የተቀመጠው ሁለተኛው ነጥብ የግል ተበዳይ ወንጀለኛውን በማበሳጨት ለወንጀሉ መፈጸም የሚያደርገው አስተዋጾ ሲሆን

[55] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 47፣ ገጽ 305።

[56] የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ፣ ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 45፣ አንቀጽ 82 (1) (ሐ፣መ፣ሠ)፡፡

[57] በቀረበው ጉዳይ ላይ እንደተመለከተው ወንጀለኛው ወንጀሉን ለመፈጸም ያነሳሳው አስጥቶት የነበረውን እኽል የንጉሡ በግ ስለበላበት ነበር። ይህንን ሁኔታ ስንመለከት ወንጀለኛው የነበረበት ሁኔታ የሚበላው ያጣና የተቸገረ ነበር ለማለት በፍጹም አይቻልም፡፡

በቀረበው ጉዳይ ላይ የንጉሡ በግ የተከሳሽን የተሰጣ እኽል መብላቱ ተከሳሹን እንዳናደደው መረዳት ይቻላል። ሦስተኛው በሕጉ የተቀመጠው ምክንያት ተከሳሹ ክሱን ማመኑ ሲሆን ይህም በቀረበው ጉዳይ ውስጥ ሙሉ በሙሉ የተሟላ ቅድመ-ሁኔታ ነው። በዚህ ዘመን የወንጀል ሕግጋት መሠረት እነዚህ ቅድመ-ሁኔታዎች ቅጣትን ለማቅለል[58] የተቀመጡ እንጂ ከወንጀል ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ ነጻ እንደማያደርጉ ከዚህ በላይ ተመልክተናል። በቀረበው ጉዳይ ወንጀለኛው በነጻ መለቀቁን የተመለከትን ሲሆን ይህም የንጉሡ ፍርድ ከዘመኑ ሕግ በተሻለ ለተከሳሹ ጥበቃ የሰጠ መሆኑን ያሳያል።

በክሱና በተከሳሽ መልስ ውስጥ በግልጽ ባይመለከትም ከዚህ ጉዳይ ጋር አብሮ የሚነሳው ሌላው ነጥብ በተከሳሹ ዕሁፉ ውስጥ ያለው "ማነኽ እንጃልኽ" በሚል የተገለጸውና የበጉ ባለቤት (ንጉሡ) ምን ታመጣለህ የሚል ትርጉም ያለው ትዕቢት አዘል መልዕክት ነው። ንጉሡ ይህንን ተከሳሹ ያሳየውን ንቀት ችላ ብለው ማለፋቸው፣ በክሱ ውስጥ አለማንሳታቸውና አለመቅጣታቸው ከዚያም አልፎ ገንዘብ ሰጥተው መሸኘታቸው ተከሳሽ ክሱን ማመኑ በዋናነት እንዲሁም ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ሌሎች ሁለት ምክንያቶች በዘመኑ ለወንጀል ኢ-ኃላፊነት መሠረቶች መሆናቸውን እንረዳለን።[59]

## 4. የማጠቃለያ ነጥቦች

የኢትዮጵያን ሕግጋት የማዘመን ተግባር በ1940ዎቹና 50ዎቹ በስፋት የተከናወነ ሲሆን[60] እነዚህ ዘመናዊ ሕግጋት በዋናነት ከአኅጉረ አውሮፓ የሕግ ሥርዓት የተቀዱ ቢሆንም በተወሰነ መልኩ የኢትዮጵያ የሕግ አስተምህሮና አሻራ የሚያንጸባርቁ ናቸው። በዝርዝር እንደተመለከትነው በ1997 ዓ.ም ተሻሽሎ የወጣው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ በስካር የተፈጸመ ወንጀል ኃላፊነት እንደማያስከትል እንዲሁም ጥፋትን ማመን፣ በንዴትና በቁሳዊ እጦት ምክንት የተፈጸመ ወንጀል ቅጣትን ለማቅለል በምክንያትነት አካትቷል።

ከዚህ ባለይ የተመለከትናቸው ሦስቱ የጎንደር ነገሥታት ፍርዶች የኢትዮጵያን ጨምሮ በዘመናዊ የወንጀል ሕግጋት ውስጥ የተካተቱና የወንጀል ኃላፊነትን የማያስከትሉ እንዲሁም ለቅጣት ማቅለያ የሚያገለግሉ ሁኔታዎች ሥር ያሉትን መርኖችንና ጽንሰ-ኃሳቦችን የያዙ ናቸው። ከእነዚህ መርኖችና ጽንሰ-ኃሳቦች መካከል በተለይ በስካር የተፈጸመ ወንጀል ከኃላፊነት ነጻ ያደርጋል የሚለው መርኅና ጥፋትን ማመን በጊዜ ሂደት ከዳበረው የአውሮፓ

[58] ከእነዚህ ቅጣትን ለማቅለል ከተቀመጡት ቅድመ-ሁኔታዎች ውስጥ ንዴትን (provocation) በተመለከተ በሥራ ላይ ያሉት ሕግጋት የሚደነግጉት እንዲሁም የተጻፉ ድርሳናት የሚያትቱት በዋናነት በግል ተበዳይ ምክንያት በተፈጠረ ንዴት የሚፈጸምን ወንጀል እንጂ በቀረበው ጉዳይ ላይ እንደተመለከተው በእንስሳት ምክንያት ስለሚፈጠር ንዴትና ይህን ተከትሎ ስለሚፈጸም ወንጀል ባለመሆኑ ፀሀፊው ጉዳዩን በስፋት መዳሰስ አስፈላጊ ነው ብሎ አላመነበትም።

[59] በዘመኑ ለነገሥታት ይሰጥ ከነበረው ክብር አኳያ እንዲሁም ከዚህ ያነሱ ጉዳዮች ለክስና ለቅጣት ምክንያት ይሆኑ እንደነበር ሲታይ ለንጉሡ "ማነኽ እንጃልኽ" ብሎ መጻፍ በቀላሉ የሚታለፍ ጉዳይ አይመስልም። ጉዳዩን በንጽጽር ይበልጥ ለመረዳት ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው የራሳቸውን የዐፄ ኢያሱን ፈረስ ልግዛ ብሎ የጠየቀው ሰው በወንጀል መከሰሱን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል፤ እንዲሁም ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው ይህ ድርጊት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 607ና ተከታዮቹ ሥር በተደነገገው መሠረት በክብር ላይ እንደተፈጸመ ወንጀል ሊቆጠር ይችላል።

[60] በእነዚህ አመታት ውስጥ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ፣ የፍትሐ ብሔር ሕግ፣ የባሕር ሕግ፣ የንግድ ሕግ፣ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓትና የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ወጥተው ሥራ ላይ መዋላቸው ይታወቃል።

አገራትና የአሜሪካ ሕግጋት በመቶ ሃምሳ አመታት ቀድሞ ኢትዮጵያዊ መሠረት የነበረው መርኅ ነው፡፡

እነዚህ በወንጀል ሕጉ ውስጥ የተካተቱ መርኖችና ጽንሰ-ኃሳቦች በምሳሌነት የሚጠቀሱ እንጂ ሌሎች ተመሳሳይ የነገሥታት ፍርዶችንና ነባር የኢትዮጵያ ሕግጋትን መሠረት ያደረጉ መርኖችና ጽንሰ-ኃሳቦች በወንጀል ሕጉና በሌሎች ሕግጋት ውስጥ መኖራቸው አይካድም፡፡ እነዚህን በነባር የኢትዮጵያ ሕግጋት ውስጥ የነበሩ የሕግ መርኖችንና ጽንሰ-ኃሳቦችን መመርመር፣ ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ በጥልቀት ማጥናት፣ ወደፊት በሚወጡ አዲስ ሕግጋት ውስጥ እንዴት ተጣጥመው ሊካተቱ እንደሚችሉና የኢትዮጵያ ሕግጋት አካል እንዲሆኑ ማመላከትና ሃሳብ መስጠት የሕግ ምሁራንና ሊቃውንት ሙያዊ ኃላፊነት እንዲሁም መልካም አጋጣሚ ነው ብሎ ይህ አጥኚ ያምናል፡፡

**Intoxication, Provocation and Necessity as Defenses of Criminal Irresponsibility in the Judgments of Emperor Iyasu, and Emperor Dawit III of Ethiopia: A Historical Reflection**

*Nega Ewunetie Mekonnen*♣

***Abstract***

*Judgments rendered before the introduction of modern justice system in Ethiopia were largely subject to the final approval and analysis of the emperors. This trend continued to some extent until 1974; in this regard the Crown Court of Haile Selassie I was the first to be mentioned. Cases brought before the emperors' courts were often criminal cases, and the judgments of the emperors reflected principles and concepts of criminal law that have been recognized in the criminal law of many countries today. This reflection presents three criminal cases brought before the courts of Emperor Iyasu, and Emperor Dawit III of Ethiopia and argues that the judgments of these two emperors are compatible with the principles of defenses of intoxication, provocation, necessity, and criminal responsibility.*

**Key words**: Intoxication, provocation, necessity, plea of guilty, judgments of emperors, criminal irresponsibility

♣ Associate Professor of Law, Bahir Dar University, School of Law. PhD Student, Bahir Dar University, Higher Diploma in Teacher Educator (Bahir Dar University, 2015), LL.M. (The University of Groningen, The Netherlands, 2008), LL.B. (Addis Ababa University, Ethiopia, 2004). The writer can be reached for comments at beleteeng@yahoo.com.